ኃይሉን ማወቅ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ማቴዎስ 9:18-26

በልብዋ። ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ፥ እድናለሁ ትል ነበረችና። —ማቴዎስ 9:21

በየዓመቱ ለእረፍት የሚሰበሰቡ የፓስተሮች ቡድን አባል ነኝ። የምናደርጋቸው ነገሮች ሁልግዜም አንድ አይነት ናቸው፡ አከባቢያችን ባለ ከፌ ቁርስ እንበላለን፣ በአከባቢያችን ባለ የመዝናኛ ስፍራ ሆኪን እንጫወታለን፣ ቀሪውን ቀን ደግሞ ታሪኮችን በማጋራት እና አንዳንችን ለአንዳንችን በመጸለይ እናሳልፋለን።

ዘንድሮም ቁርሳችንን በልተን ለመውጣት በዝግጅት ላይ ሳለን አስተናጋጃችን ክርስቲያኖች መሆናችንን ከንግግራችን እንዳወቀች ግልጽ ነበር። ጠረጴዛችን ላይ አስቀመችንና "ከመሄድህ በፊት እንድትጸልይልኝ እፈልጋለው ነገ ማጨስን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አቆማለው እና በራሴ ማድረግ እንደማልችል አውቃለሁ። እባክህ አምላክ እንዲረዳኝ ጠይቅ" አለችን።

እኛም ተሰብስበን ነጻ እንድትወጣ አጥብቀን ጸለይን። ሙሉ በሙሉ ታሪኳን አላውቀውም፣ ነገር ግን ኢየሱስ በዚያን ወቅት በመካከላችንና ከእርሷ ጋር እንደነበር እና ልጆቹ ነጻ ሲወጡ ማየት እንደሚፈልግ አውቃለሁ።

ይህ ዓይነቱ ነገር በኢየሱስ አገልግሎት የተለመደ ነበር። ሰዎች በዕለት ተዕለት ትግላቸው ሊረዳቸው እንደሚቻል ተገንዝበው ነበር። በዛሬው የቃል ምንባብ ላይ እንዳለችው ሴት፣ ኢየሱስን ለመያዝ እና ለመፈወስ ሁሉን ለማድረግ ፈቃደኛ ነበሩ።

በእኛ ዙሪያ ያሉ ሰዎች የኢየሱስን ሃይል እና ፍቅር ይሰማቸው፤ እኛም ለሰዎች መፈወስ ለመጸለይ ድፍረት እና አቅም ያለን ያድርገን።

ጌታ ሆይ በሓይልክ በመካከላችን እየሰራክ ስላለክ አመሰግንሃለሁ። በህይወታችን ውስጥ የተበላሹ ነገሮች ፈውስ ያግኛቸው፤ በመንገዳችን ለሚያጋጥሙን የተጎዱ ሰዎች በምንጸልይ ግዜ ጸሎታችንን ስማ በሐይልክ ፈውሳቸው። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/)** ድሕረ ገጽ ተወስዶ ተተረጎመ

ንቁ ! ተነሱ!

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ሉቃስ 7:11-17

ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም። አንተ ጐበዝ፥ እልሃለሁ፥ ተነሣ። —ሉቃስ 7:14

እኔ የጠዋት ሰው አይደለሁም፤ ብሆን እመኛለሁ። እንደ አስፈላጊነቱ ማልጄ መነሳትን ተምሬያለሁ፣ ነገር ግን እንድነቃ የተወሰነ ጊዜ እና ቡና መጠጣእ አለብኝ።

ዛሬ ከሉቃስ 7 ላይ ባለው ንባባችን አስደናቂ መነሳትን እናያለን። አንድ ወጣት ሞቷል፤ ኢየሱስ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ተመልክቶ ልቡ መበለት የሆነችውን የወጣቱን እናት ልቡ አሰበ። ወደ ቀብር ቦታው ሄዶ "አንተ ወጣት፣ እልሃለሁ፣ ተነሳ!" አለው። ኢየሱስ እዚህ ላይ የተጠቀመው የግሪክኛ ቃል ቀጥተኛ ፍቺው "ንቃ" ማለት ነው። ኢየሱስ ወጣቱን እንዳልሞተ ነገር ግን እንደተኛ አድርጎ ነው ያዘዘው፤ ከእንቅልፉ ሲነቃ ወጣቱ ማውራት ይጀምራል። ይህም ለማካተት አስቂኝ ሃሳብ ይመስላል ምናልባት የጠዋት ሰው ሊሆን ይችላል!

በዚህ ምንባቡ ውስጥ ወረድ ብለን ስንመለከት ተመሳሳይ ቃል እንደገና ጥቅም ላይ ይውላል፤ ይህን ተአምር ያዩ ሰዎች "ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ታየ" ብለው በፍርሃት አወጁ። ይህ ቃል በቃል ሲተረጎም "ታላቅ ነቢይ በመካከላችን ነቅቷል!" ማለትም ሕዝቡ ከአምላክ በተለየ የተላከ ሰው ፊት እንዳሉ ማየት ችለዋል። ስለ ኢየሱስ ገና ብዙም አያውቁም ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ይማራሉ።

የጠዋት ሰው መሆንዎን ወይም አለመሆኖን አላውቅም፣ ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ ልናቀርበው የምንችለው ጠቃሚ ጸሎት እዚህ አለ፡- "ኢየሱስ ሆይ፣ እባክህ አንቃኝ!" በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች ለማየት እና ለመንከባከብ ጌታ እንዲነቃህ ጠይቅ።

አባት ሆይ! በዚያ ወጣት ውስጥ የትንሳኤ ሃይልህን እንደሰራህ፣ ዛሬ በህይወቴ እና በመንፈሴ ተመሳሳይ ሃይል እንድትሰራ፤ በታማኝነት እንዳገለግልህ ጸጋህ እንዲረዳህ እለምንካለው። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/)** ድሕረ ገጽ ተወስዶ ተተረጎመ

በጸሎት መድረስ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ዮሐንስ 17:20-23

ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።— ዮሐንስ 17:20-21

ጥሪያችን - ተልእኳችን - የሚጀምረው በጸሎት ነው። እግዚአብሔር በጸሎት በኃይል ይሠራል፣ ሁልጊዜ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ትችላላችሁ። በቀን ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ከጌታ ጋር ጊዜ ማሳለፍ ትችላለህ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ከሚታወቁ ጸሎቶች በአንዱ በዮሐንስ 17 ላይ ኢየሱስ ስለ አንተና ስለ እኔ ጸልዮአል። እርሱ ወደ እኛ ሲደርስ ማየት ምንኛ የሚያጽናና ነው፤ በጸሎት ሕይወታችንም ለእኛ አርአያችን ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች እና አብያተ ክርስቲያናት የጸሎት ጥያቄዎችን በመደበኛነት ይቀበላሉ። በህይወታችሁ ውስጥ ለጎረቤቶች ወይም ለሌሎች መጸለይ፣ ለጥያቄም ሆነ አጠቃላይ በረከት፣ በጌታ ስራ ለመሳተፍ ታላቅ መንገድ ነው። ነገር ግን የጸሎት መሪ እንድትሆኑ ላበረታታችሁ እፈልጋለሁ። ሌሎችን ማግኘት እና "እንዴት ለእናንተ መጸለይ እችላለሁ?" ሰዎች  መስማት የሚያስፈልጋቸው ጥያቄ ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔርን ተልዕኮ መቀላቀል ማለት ወደ ሌላ ክልል ወይም ሀገር መሄድ ብቻ ማለት አይደለም; በገዛ ሰፈራችሁ ሚስዮናዊ መሆን ትችላላችሁ!

ብዙ አማኞች ሃይማኖተኛ ያልሆኑ የሚመስሉ ሰዎች እንድንጸልይላቸው ስንጠይቃቸው ብዙውን ጊዜ ፈቃደኛ ሲሆኑ ይገረማሉ፤ ከሌሎች ጋር የጸሎት አካል መሆን በአንተ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድም እንደሚታዩ ያስታውሳቸዋል።

አባት ሆይ፤ ወደ እኔ ስለደረስክ; ከሌሎች ጋር እንድገናኝ ስለረዳከኝ አመሰግንካለው። ጸሎት የሚያስፈልጋቸውን ጎረቤቶቼን እንድመለከት እርዳኝ ቤተ ክርስቲያንህ እንድታድግ እና ሕዝብህ አንድ እንዲሆኑ እንደሚገባ እንዳገለግል አግዘኝ። አሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ ተተረጎመ

በእኔ ውስጥ ቆዩ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ዮሐንስ 15: 1-8

እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። — ዮሐንስ 15: 5

በኢየሱስ 'መቆየት' የምንችለው እንዴት ነው?

ከጸሎት ጋር ብዙ የሚያገናኘው ነገር ያለ ይመስለኛል። ያደግኩት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፣ እናም ወጣት ሳለሁ ጸሎት ሁል ጊዜ አሰልቺ ይመስለኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። ፓስተሩ ረጅም ሲጸልይ አይኖቻችንን ጨፍነን፣ አንገታችንን ደፍተናል እጆቻችንን እናጨበጭባለን። ነገር ግን እያደግኩ ስሄድ ኢየሱስ ይበልጥ እውን ሆኖልኛል፣ የጸሎት ሕይወቴ መለወጥ ጀመረ።

እጃችንን ማጠፍ እና ዓይኖቻችንን መጨፈን ምንም ችግር የለውም - አሁንም አንዳንድ ጊዜ ትኩረት ለማድረግ ያንን ማድረግ እወስዳለሁ። ነገር ግን በእምነት እያደግኩ ስሄድ፣ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ስለማሳለፍ የበለጠ ሆኖ አገኘውት። እግዚአብሔርን ማመስገን እና ልመናዬን ወደ እርሱ ማንሳት ብቻ አልተማርኩም፤ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና መንፈስ የሚናገረውን ለማዳመጥ ጊዜ ማሳለፍንም ተማርኩ።

ከኢየሱስ ጋር በጸሎት ጊዜ ማሳለፌን ቀጠልኩ በዚህም በሕይወት ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥም እንኳ ስሆን ይበልጥ ታጋሽ ሰው መሆኔን ተረድቻለሁ፤ በጣም ብዙ ለመስራት በሚቻልባቸው ቀናት፣ ለቤተሰብ እና ለጓደኞቼ በምሰጠው ምላሽ ደግ እና ቀርፋፋ የመሆን እድሌ ሰፊ ነበር። በተጨማሪም አካባቢዬ ካሉ ጎረቤቶች ጋር ለመነጋገር ጊዜ እሰጣለሁ፤ እናም የመንፈስ ቅዱስን መነሳሳት ለመፈለግ እና ምላሽ ለመስጠት የበለጠ እድል ኖረኝ።

ጌታ ሆይ፣ በአንተ ፊት በጸሎት ጊዜ ለማሳለፍ ስለቻልን እናመሰግናለን። ፍቅርህ እና ፀጋህ እንተን እንድንመስል እንድንለውጥና ከአንተ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ሆን ብለን እንድናስብ እርዳን። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ ተተረጎመ

የህይወቴ ጸሎት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ፊልጵስዩስ 3: 10-11

ክርስቶስን ማወቅ እፈልጋለሁ። . . . —ፊልጵስዩስ 3:10

በአውሮፓ ያሉ ተመራማሪዎች ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ ሰዎችን በአምላክ ላይ ያላቸውን እምነት ይጠይቁ ነበር። አንዱ ጥያቄ "በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ በሚገባ፣ ታሪክን በሚቀይርና ተአምራትን በሚሠራ አምላክ ታምናለህ?" የሚል ነበር። ለዚህ ጥያቄ የተለመደው ምላሽ "አይ፣ በዚያ አምላክ አላምንም፣ በተለመደው አምላክ አምናለሁ" የሚል ነበር።

"የተለመደው አምላክ" ማለትም እሱን በሚያስፈልገኝ ጊዜ እዚያ የሚገኘውን ነገር ግን በሕይወቴ ውስጥ በምሠራበት ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ ጸጥ የሚለኝን አምላክ መምረጥ ፈታኝ እንደማይሆንብኝ አልክድም።

ደግነቱ ቅዱሳት መጻህፍት በተለመደው አምላክ አስተሳሰብ እንድንስማማ አይፈቅዱልንም። በአዲስ ኪዳን ያገኘነው ኢየሱስ ወደ ዓለማችን ገባ፣ የኃጢያት ሸክማችንን በመስቀል ላይ ተሸክሞ፣ በእኛ ቦታ ሞተ፣ ከዚያም ከሙታን ተለይቶ ተነስቶ በኋላም ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ ሊገዛ አረገ። ይህ የተለመደ አምላክ አይደለም።

የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ በሚያስደንቅ፣ በሚያምር እና ባልተለመዱ መንገዶች ወደ ህይወታችን ይመጣል። እውነተኛው አምላክ ከእኛ ከአቅም ልክ በላይ ነው። ይህ ሁሉ በጳውሎስ አስደናቂ ጸሎት ላይ "ክርስቶስን ማወቅ እፈልጋለሁ—አዎ፣ የትንሣኤውን ኃይል ማወቅና በሥቃዩም ውስጥ መካፈሉን ማወቅ እፈልጋለሁ" ከዚያም ትንሣኤን ማግኘት እፈልጋለሁ በማለት አካቶታል።

እንዴት ያለ ጸሎት ነው! ይህ የሕይወቴ ጸሎት ከሆነ ሕይወቴ እንዴት ይለወጣል? በሕይወቴ ውስጥ ላሉ ሰዎች ይህን ብጸልይ ምን ሊሆን ይችላል?

አባት ሆይ፣ ላውቅህ እፈልጋለሁ። የትንሣኤህን ኃይል እንድለማመድ እርዳኝ። አሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ ተተረጎመ